
‹‹ከከተማው አስተዳደር ጋር ተነጋግረን በተደረገልን ድጋፍ የራሳችን መዝናኛ ካፌም ከፍተን ነበር፡፡ ይህን ያደረግነው ክበባችን የራሱ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው በማሰባችን ነው፡፡ የጎዳና ተዳዳሪዎችን የመዝናኛ ክበቡ ሠራተኞች በማድረግም እንዲታገዙበት አድርገናል፡፡ እዚያው እንዳለ ወጣቶች አልባሌ ቦታ እንዳይውሉና እንዲዝናኑበት ያደረገ ክበብ ነበር፡፡

‹‹በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለን አማራ አቀፍ ልማት ማህበር በየወረዳው ያሉ ክበቦችን እያወዳደረ የተሻሉትን ይሸልም ነበር፡፡ አልማ የእኛን እንቅስቃሴ የተሻለ ሆኖ አገኘው፡፡ ከዚህ በኋላም ድጋፍ ያደርግልን ጀመር፡፡ የአመራር፣ የወጣቶች ተዋልዶ፣ የሥራ ፈጠራ፣ የቴአትርና የሙዚቃ፣ የኮምፒዩተር ክህሎት፣ የአቻ ለአቻ መማር፣ ማህበረሰብን ስለሚያሳትፍው ይይትና ሌሎችም የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ሰጥቶናል፡፡ በቁሳቁስ ረገድም ቴፕ ሪከርደር፣ ቴሌቪዥን ከዲ ኤስ ቲቪ መስመር ጋር፣ የክሊኒክ እቃዎችና የስፖርት ትጥቆች አበርክቶልናል፡፡ ከአልማ የተሰጡን ቼዝ፣ ዳርትና የጠረጴዛ ቴኒስን የመሳሰሉት የቤት ውስጥ መጫዎቻዎችም ነበሩን፡፡ ለአንድም ጊዜ ያልተለየን የሃሳብና የሞራል ድጋፉ ደግሞ ከሁሉም የላቀ ነበር፡፡››

— // —




*አቶ ያሬድ ሙላት*
*የቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ ልማት ድርጅት የፕሮጀክት አስተባባሪ*

‹‹ቤዛ መጀመሪያ ክበብ ነበረ፡፡ በኋላ ግን በሕግ ተመዝግቦ የሚሠራ ማህበር ሆነ፡፡ ማህበር ከሆንን በኋላም የአልማ ድጋፍ አልተለየንም፡፡ በየሩብ ዓመቱ የሚለቀቅ መደበኛ በጀት መድቦልን ሥራችን እዲጠናከር አድርጓል፡፡ በዚህ ጊዜ የማቴሪያል ድጋፍ ማድረጉንም ቀጥሏል፡፡ የቢሮ ዕቃዎችን በሙሉ ያሟላልን አልማ ነው፡፡ የመረብ ኳስና ተጨማሪ የጠረጴዛ ኳስ ቁሳቁሶችንም ሰጥቶናል፡፡

በዚህ ጊዜ አልማ ድጋፍ የሚያደርግላቸው በአማራ ክልል 10 ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ ክበቦች ነበሩ፡፡ አልማ እነዚህ ሌሎች ክበቦች ከእኛ ልምድ እዲቀስሙና እንዲማሩ በመፈለጉ ኮምቦልቻ ከተማ ላይ ፌስቲቫል እንድናዘጋጅ ትልቅ ድጋፍ አድርጎልናል፡፡ ፌስቲቫሉ ለሰባት ቀናት የተካሄደ ነበር፡፡ በዚህ ፌስቲቫል በሁለቱም ፆታዎች የሩጫና የመረብ ኳስ የስፖርት ውድድሮች ተደርገዋል፡፡ በኪነ ጥበብም የሙዚቃ፣ የቴአትር፣ የሥነ ፅሁፍና የባሕል ዝግጅቶች ቀርበው ነበር፡፡ የቢሮ ጉብኝትም የተደረገ ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ የወሰደው ግን እያንዳንዱ የፌስቲቫሉ ተካፋይ ወረዳ የሥራ ልምዱን እያቀረበ የተማማርንበት የፓነል ውይይት ነው፡፡

‹‹በክበብም ሆነ በማህበር ደረጃ ተደራጅተን የሠራነው ሥራ እጅግ በጣም አርኪ ነበር፡፡ የወጣትነት ዘመናችን ማክተሚያ እየደረሰ ሲመጣ ግን በዚያው ልንቀጥል እንደማንችልና እንደማይገባ ተረዳን፡፡ በዚህም፣ መንግሥታዊ ወዳልሆነ ድርጅት የመሸጋገር ሃሳብ አደረብን፡፡ በቅድሚያ ግን በሁለት ወረዳዎች ውስጥ በወጣቶች ላይ ያተኮረ ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከል የሙከራ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ቀረፅን፡፡ የፕሮፖዛሉ ትኩረት መታቀብና መወሰን ላይ ሲሆን፣ ለሙከራ እንቅስቃሴያችን ድጋፍ ያደረገልንም ፓክት ኢትዮጵያ ነበር፡፡ በአፈፃፀማችን ከሌሎች የተሻልን ሆነን በመገኘታችንም በሚቀጥለው



ወይዘሮ ሐሊማ ይመር
የቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ ልማት ድርጅት አካውንታንት

ዓመት በአሥር ወረዳዎች ውስጥ እንድንሠራ ፈቀደልን፡፡ ራሳችንንም መንግሥታዊ ወዳልሆነ ድርጅት አሳደግን፡፡ የማህበራችን ሥምም በሌላ ተተካ፡፡

‹‹ድርጅታችን ‹ቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ የልማት ድርጅት› ይባላል፡፡ በእንግሊዝኛው ቋንቋ ‹ፖስቴሪቲ› ማለት ‹መጪው ወይም የወደፊቱ ትውልድ (Future Generation) ማለት ነው፡፡ በወጣትነታችን እንሰራው የነበረው የማህበር ሥራ አልተቋረጠም፡፡ ሌሎች ወጣቶችን ተክተናል፡፡ ‹ቤዛ ለወገን ማህበር› ይባላሉ፡፡ በእኛ ሥር ሆነው ነው የሚሠሩት፡፡ ድርጅታችን በማቴሪያል፣ በገንዘብ፣ በስልጠናና በማያቋርጥ ክትትል ይደግፋቸዋል፡፡

‹‹በድርጅታችን ቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ የልማት ድርጅት ውስጥ ቋሚ ሆነን የምንሠራው ሠራተኞች 10 ነን፡፡ ሁላችንም የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር (አልማ) አባሎች ነን፡፡ አሁን የወጣት ለወጣቶች ክሊኒክ አለን፡፡ አልማ ነበር ያቋቋመልን፡፡ ለክሊኒኩ የገንዘብ ድጋፍ እያደረገልንም ቆይቷል፡፡ አሁንም ልማት ተኮር የቴአትር (Theater for Development) ፕሮፖዛል ቀርፀን ለአልማ አቅርበን መልሱን በመጠበቅ ላይ ነን፡፡

‹‹እዚህ ደረጃ ለመድረስ ያስቻለን ቀኝ እጃችን አልማ ነው፡፡ የክልላችን ከፍተኛ የልማት አጋር ከመሆን አልፈን፣ በሌሎች ክልሎችም መሥራት ወደምንችልበት ደረጃ መድረሳችን አይቀርም፡፡ ወደፊትም የአልማ ድጋፍ እንደማይለየን ሙሉ እምነታችን ነው፡፡››

*አሥሩ የቤዛ ፖስቴሪቲ ኢትዮጵያ ልማት ድርጅት ቋሚ ሠራተኞች*




# አልማ በማሕበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት

ስዎች ሁሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች ተሟልተው የማየትና የመጠቀምን ያህል የልባቸውን የሚያደርስ ጉዳይ እንደሌለ አብዛኛዎቻችንን የሚያስማማ ይመስለኛል። እንዲህም ሆኖ ግን “መሰረታዊ አገልግሎቶች ተሟልተዋል የምንለው ምን ምን ተሟልቶ ሲገኝ ነው? አገልግሎቶቹስ ሲጓደሉ ለሟሟላት ምን ዘዴ መዘየድን ግድ ይለናል?” ለሚሉት መጠይቆች በዚህ አጭር ጹሁፍ ሙሉ መልስ ማግኘት አይቻል ይሆናል። ይሁን እንጂ በመንግስትና ህዝብ አዲስ አጋርነትን በመፍጠር ላይ በሚገኘው በከለላ ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ለሕብረተሰብ ተጠያቂነት አዲስና የሙከራ ፕሮጀክት ሕብረተሰቡ በየአካባቢው ስለሚያገኘው መሠረታዊ አገልግሎት ለሙከራ በተመረጡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እና ጤና አገልግሎቶች ዙሪያ የእነዚህን መሠረታዊ የሚባሉ አገልግሎቶችን ተገቢነት ሕብረተሰቡ እንዴት እንደፈ‧ተሸ፣ ድምጹን ማሰማት እና አገልግሎቶቹ በሚሰጡበት ተቋማት በአካል በመገኘት ነቅሶ ያወጣቸውን ችግሮች በጋራ ለመፍታት ከአገልግሎት ሰጪዎችና ከውሳኔ ሰጪ አካላት ጋር ገፅ ለገፅ/ግንባር ለግንባር በመወያየት የጋራ መግባባት ላይ ሥለመድረሳቸው በዚህ ፁሁፍ መዳሰስ ይቻላል።

ለመግቢያ ያህል ይህን ካልን፣ ከለላ ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ሥንል ምን ማለታችን እንደሆነ፣ መቸ እንደተጀመረና በውስጡ ያሉትን ዘርፎች ከማየታችን በፊትም ቢሆን ለዚህ አጭር ቅኝት ሲባል የጹሁፉ አቅራቢ መሠረታዊ አገልግሎቶች የሚባሉት የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃ እና እርሻ አገልግሎቶችን ማለቱ መሆኑን አንባቢዎች ልብ እንዲሉለት ይጠይቃል።

ድህነትን ለመቀነስና ያልተማከለ ህዝባዊ አገልግሎት በዝቅተኛ የኑሮ



ደረጃ ለሚገኘው የሕብረተሰብ ክፍል ለማቅረብ እንዲያስችል የልማት አጋሮች “ከለላ ለመሰረታዊ አገልግሎቶች” በሚል መንገድ ለማስተዋወቅ ጥረት እያደረጉ ነው። ከለላ ለመሰረታዊ አገልግሎቶች (PBS) አራት ዋና ዋና ዘርፎችን የያዘ ፕሮጀክት ነው። እነሱም:-